# በግብርና ሚኒስቴር
# እና
# ጥጋብ አግሮ ኢንዱስትሪ መካከል የተፈፀመ
# የመሬት ኪራይ ውል ስምምነት

ይህ የመሬት ኪራይ ውል ስምምነት በግብርና ሚኒስቴር አድራሻው በቦሌ ክ/ከተማ አዲስ አበባ ; ኢትዮጵያ የሚገኝ መሆኑ እና ከዚህ በኋላ ‹‹አከራይ›› በመባል በሚታወቀው

እና

*ጥጋብ አግሮ ኢንዱስትሪ* ከዚህ በማስከተል ‹‹ተከራይ›› በመባል የሚጠቀሰው በኢትዮጵያ ንግድ ህግ መሰረት የተቋቋመና የተመዘገበ፣ አድራሻው *አዲስ አበባ ከተማ* አስተዳደር *ንፋስ ስልክ ላፍቶ* ክፍለ ከተማ *04/05* ቀበሌ የቤት ቁጥር *አዲስ* ስ.ቁ *0911 37 49 07/0910 63 60 87* መካከል ተፈፅሟል። ተከራይ የሚለው አባባል እንደ አገባቡ የማህበሩን ተተኪዎች/ወራሾች እንዲሁም ወኪሎች የሚመለከት ነው።

ተከራይ በጥጥና በተፈራራቂነት ሰሊጥና ሌሎችን የቅባት ሰብሎች ልማት ለመስማራት *በቤንሻንጉል ጉሙዝ* ክልል ውስጥ ለልማቱ በቂ የሆነ መሬት በመፈለጉ፣

አከራይ አስፈላጊውን መሬት ቀጥሎ በተዘረዘሩት የውል ቃሎችና ሁኔታዎች መሰረት ለተከራይ ለመስጠት ፈቃደኛ በመሆኑ፤

ተዋዋይ ወገኖች *በ 23/11/2003* ዓ.ም ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የውል ቃሎች እና ሁኔታዎች መሰረት ይህንን የመሬት ሊዝ ስምምነት ፈጽመዋል።

## አንቀጽ 1
## የስምምነቱ ወሰን

1.1 የዚህ የሊዝ ስምምነት ወሰን በረዥምም ጊዜ የመሬት ሊዝ *በቤንሻንጉል ጉሙዝ* ክልል *መተከል* ዞን *ዳንጉር* ወረዳ *ቆታ* ቀበሌ ውስጥ በ *3,000* ሄ/ር መሬት *የጥጥና በተፈራራቂነት የቅባት ሰብሎች* እርሻ ለማቋቋም ነው። መሬቱም በዚሁ አግባብ የሚከራየው መሬቱን በአግባቡ የመጠቀም እንዲሁም በመሬቱ ላይ የሚገኙ፣ መዋቅሮች፣ ተከላዎች፣ ንብረቶች እና ሌሎች በመሬቱ ላይ የሚደረጉ ማሻሻያዎችን ለስራው ዓላማ ተግባራዊ ማድረግን የሚያካትት በመሆኑ፣

1.2 ይህ የመሬት ኪራይ ስምምነት ከዚህ በማስከተል "የኪራይ መሬት" በመባል የሚጠቀሰውን የገጠር መሬት ሙሉ በሙሉ እና በብቸኝነት ለመጠቀምና በዚህ ስምምነት በአንቀጽ ሁለት በግልጽ የተቀመጠውን የኪራይ ክፍያ ብቻ ለመክፈል የተፈፀመ ነው።

ጥጋብ አግሮ ኢንዱስትሪ
Tigab Agro-Industry

ግብርና ሚኒስቴር
Ministry of Agriculture

## አንቀጽ 2

## የኪራይ ዘመን እና በተከራየው መሬት ተከፋይ የሚሆነው የሊዝ ክፍያ

2.1 ይህ የመሬት ኪራይ ስምምነት ለ 25 ዓመታት የፀና ይሆናል። ሆኖም በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ለተጨማሪ አመታት ሊታደስ ይችላል።

2.2 የመሬት ኪራይ ክፍያ አፈፃፀም፦

2.2.1 ይህ ስምምነት ከተፈረመበት ቀን አንስቶ የመሬት ኪራይ ክፍያ የ 3 ዓመት የዕፎይታ ጊዜ ያለ ሲሆን በዕፎይታ ጊዜው ያልተከፈለው የመሬት ኪራይ ክፍያ ከዕፎይታ ጊዜው በኋላ ባሉት ዓመታት እኩል ተካፍሎ በየዓመቱ ከመደበኛው ጋር የሚከፈል ይሆናል።

2.2.2 ከዚህ በኋላ በዚህ ውል በአንቀጽ 1 ለተጠቀሰው የግብርና ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ለእያንዳንዱ ሄክታር የብር232.5 ( ብር ሁለት መቶ ሠላሳ ሁለት ከሃምሳ ሳንቲም ብቻ ) የኪራይ ክፍያ ይፈፀማል። በዚህ መሰረት በየዓመቱ ብር 697,500 (ብር ስድስት መቶ ዘጠና ሰባት ሺህ አምስት መቶ ብቻ) የሚከፈል ሲሆን የዚህ ውል ዘመን ጠቅላላ የኪራይ ክፍያ መጠን ብር 17,437,500 ( ብር አስራ ሰባት ሚሊዮን አራት መቶ ሰላሳ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ብቻ ) ይሆናል።

2.2.3 በዚህ ውል አማካኝነት ተከራይ የመሬት ኪራይ ክፍያ ሲከፈል የክፍያው ደረሰኝ ወዲያውኑ ሊሰጠውና ቅጅው/ኮፒው ለወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት መቅረብ አለበት።

2.2.4 በዚህ አንቀጽ ላይ በቁጥር 2.2.1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከላይ ለተገለጸው መሬት የአንድ አመት ቅድሚያ ክፍያ ተፈጻሚ ይሆናል።

2.2.5 አስፈላጊ በሆነ ጊዜ አከራይ የመሬት ኪራይ ተመኑን ለተከራይ በማሳወቅ ሊያሻሽል ይችላል፤

## አንቀጽ 3

## የተከራይ መብቶች

ተከራይ ከዚህ የሚከተሉት መብቶች አሉት፦

3.1 መሬቱን ስምምነት በተደረሰበት አግባብ ማልማት እና በስምምነቱ ቃሎች መሰረት ማስተዳደር፤

3.2 በኢንቨስትመንት ፕሮጀክቱ ዓይነት እና መጠን እንዲሁም እንደ አግባብነቱ በሚመለከታቸው መ/ቤቶች የፈቃድ ጥያቄ በማቅረብ እና ምክክር በማድረግ እንደ ግድብ፤ የውሃ ጉድጓድ፤ የሀይል ማመንጫ፤ የመስኖ ሲስተም፤ መንገዶች፤ ድልድዮች፤ ጽ/ቤቶች፤ የመኖሪያ ህንፃዎች፤ የነዳጅ ማደያ፤ የጤና እና የትምህርት ተቋማት የመገንባት፤ በዚህ ሂደት ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች አስፈላጊ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት በመተባበር ይሰራል።

3.3 የተከራየውን መሬት በራሱ ወይም በህግ አግባብ በውክልና በተሾመ ሰው/ድርጅት የማልማት ወይም የማስተዳደር፣

3.4 በዘመናዊ መሳሪያና ሌሎች አግባብነት ባላቸው መንገዶች በመጠቀም መሬቱን የማልማት እና የማረስ፣ ምርትን የመሰብሰብ፣

3.5 በድርጅቱ ስራ አፈፃፀም፣ ስኬትና ፍላጎት ላይ በመመስረት ተጨማሪ መሬት ማግኘት፣

3.6 አሳማኝ በሆነና ለተሻለ ነገር ለአከራይ ከስድስት ወር የማያንስ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ኪራይ ስምምነቱን መሰረዝ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 4

## የተከራይ ግዴታዎች

4.1 ተከራይ ለተከራየው መሬት መልካም እንክብካቤ የማድረግ እና በመሬቱ ላይ የሚገኙ ሀብቶችን የመጠበቅ ግዴታ ያለበት ሲሆን በተለይም ከዚህ የሚከተሉት ግዴታዎች በተከራይ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡-

ሀ. በመሬት ዝግጅት ወቅት ሳይመነጠሩ የቀሩትን ዛፎች መጠበቅ፤

ለ. ተዳፋትነት ባለባቸው አካባቢዎች የአፈር መሸርሸርን ለመከላከል አግባብነት ያላቸው የአሰራር ዘዴዎችን መጠቀም፣

ሐ. ስለ ተፈጥሮ ሀብቶች አጠባበቅ በህግ የተደነገጉ ግዴታዎችን ማክበር እና እነዚህንም በጠቅላላው ተግባራዊ ማድረግ

መ. ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት በማካሄድ የጥናት ሪፖርቱን የኢንቨስትመንት መሬት ርክክብ በተፈፀመ ከአራት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ማቅረብ፡፡

4.2 ተከራይ ውል በተፈጸመ በ30 ቀናት ውስጥ በንዑስ አንቀጽ 2.2.4 ተተቀሰውን ቅድሚያ ክፍያ በመክፈል መሬቱን መረከብ አለበት፡፡

4.3 ከመንግስት እንዲሁም ከሌሎች ኤጀንሲዎች አግባብነት ያላቸው ፈቃዶች የተሰጡ እንደሆነ ይህ የኪራይ ስምምነት ከተፈረመበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር የ6 ወራት ጊዜ ውስጥ ተከራይ መሬቱን ማልማት መጀመር አለበት፡፡

4.4 በዚህ የውል ስምምነት ስር ተከራይ ይህ የመሬት ኪራይ ስምምነት ውል ከተፈረመበተ ቀን አንስቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የመሬቱን *1/3ኛ* ክፍል የማልማት ግዴታ አለበት፡፡ በመሆኑም በጠቅላላው የተከራየውን መሬት ይህ ስምምነት ከተፈረመበት ቀን አንስቶ *ከ3* ዓመታት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የማልማት ግዴታ አለበት፡፡

4.5 የመሬት ኪራይ ውሉ የተፈፃሚነት ጊዜ ሲያበቃ ወይም ሲቋረጥ ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃዱ ሲሰረዝ ተከራይ በመሬቱ ላይ የተተከሉ ንብረቶችን በአግባቡ በማንሳት ከ6 ወራት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መሬቱን ለአከራይ ያስረክባል፡፡

4.6 ተከራይ ለግብርና ሚኒስቴር በሚቀርብለት ጥያቄ መሰረት ትክክለኛ መረጃ እና የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ሪፖርቶች ያቀርባል።

4.7 የዕፎይታ ጊዜው እንደተጠናቀቀ  የወቅቱን አመታዊ የመሬት ኪራይ ክፍያ በዕፎይታ ጊዜው ያልተከፈለውን ድርሻ በመጨመር መሬቱ ለሚገኝበት ክልል ከታህሳስ ወር አንስቶ እስከ ሰኔ ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ቀደም ሲል ለገጠር መሬቶች ተፈፃሚነት እንዲኖረው በተወሰነው የኪራይ ተመን መሰረት ክፍያ ይፈፅማል።

4.8 ተከራይ ይህንን የመሬት ኪራይ ውል ሲፈጽም ከዚህ የውል ሰነድ ጋር በማያያዝ የተከራየውን መሬት አጠቃቀም የድርጊት መርሃ ግብር ለግብርና ሚኒስቴር ያቀርባል።

4.9 በጽሁፍ በሚቀርብ ጥያቄ መሠረት የአከራይ ፈቃድ ሳይሰጥ ተከራይ በየትኛውም ሁኔታ ቢሆን መሬቱን ላልተፈቀደለት እና ቀደም ሲል በአንቀጽ 3 ላይ ላልተቀመጠ ዓላማ ወይም እቅድ መጠቀም አይችልም።

4.10 ተከራይ በማህበር ስም የተከራየውን መሬት በግል ለማልማት ሲባል ለማህበሩ አባላት ማከፋፈል  እና ለሶስተኛ ወገን ማከራየት አይችልም። ሆኖ ቢገኝ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የመሬት ኪራይ ውሉ እንዲቋረጥ ያደርጋል።

4.11 የመሬቱ 75 በመቶ ሳይለማ ድርጅቱ መሬቱን ለሌላ ድርጅት ወይም ግለሰብ አሳልፎ የመስጠት መብት አይኖረውም።

4.12 ተከራይ የመሬቱን 75 በመቶ በማልማትና የአከራዩን ፈቃድ ካገኘ መሬቱን ለሌላ ድርጅት ወይም ግለሰብ ማዛወር ይችላል። አከራይ ጥያቄ በቀረበ ጊዜ አፋጣኝ ምላሽ ይሰጣል።

4.13 ይሁን እንጅ ተከራይ ከላይ በንዑስ አንቀጽ 4.11 የተሰጠው መብት ቢኖርም ያላለማውን መሬት ለሌላ ወገን ማዛወር አይችልም።

## አንቀጽ 5

## የአከራይ መብቶች

አከራይ ከዚህ የሚከተሉት መብቶች ብቸኛ ተጠቃሚ ይሆናል፡-

5.1 ተከራይ ግዴታዎቹን በትጋት መወጣቱን እና መፈፀሙን የመቆጣጠር እና የመከታተል መብት ይኖረዋል።

5.2  መሬቱ በኪራይ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ የአንድ አመት ጊዜ ሲያበቃ በንዑስ አንቀጽ 4.3 መሰረት ያልለሙትን መሬቶች ይወስዳል። ይህም ተፈፃሚ የሚሆነው ተከራይ የ6 ወራት ቅድመ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት በአንድ አመት ውስጥ ሳያስተካክል የቀረ እንደሆነ ነው።

5.3  አከራይ ከላይ በአንቀፅ 5.1 የተሰጠውን መብት በሚጠቀምበት ወቅት የተከራዩን ተግባራት እና እንቅስቃሴዎች በማያውክ ሁኔታ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

5.4 አሳማኝ በሆነና ለተሻለ ነገር ለተከራይ ከስድስት ወር የማያንስ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ኪራይ ስምምነቱን መሰረዝ ይችላል፡፡

5.5 በዚህ የመሬት ኪራይ ውል በተገለፀው መሰረት የመሬት ኪራይ ዋጋ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

## አንቀፅ 6

## የአከራይ ግዴታዎች

6.1 አከራይ መሬቱን ከማናቸውም ለሥራው እንቅፋት ከሆኑ ነገሮች እና ሌሎች እክሎች ነፃ በማድረግ ይህ የመሬት ኪራይ የውል ስምምነት ከተፈረመበት ቀን አንስቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የማስረከብ ግዴታ አለበት፡፡

6.2 የሚከናወነውን ከፍተኛ የኢንቨስትመንት ስራ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተከራይ ከግብር ነፃ የመደረግ፣ ከገቢ የካፒታል እቃዎች የቀረጥ ነፃ እና ለውጭ ካምፓኒዎች በኢትዮጵያ ሕግጋት በሚፈቀደው መሠረት ካፒታልን እና ትርፎችን ወደ ውጭ ሃገር ስለመላክ የተቀመጡትን ልዩ ጥቅማጥቅሞች የማስጠበቅ እና የመፈፀም ግዴታ አለበት፡፡

6.3 አከራይ በተከራይ በኩል የሚያከናውነውን የመሬት መመንጠር ተግባር በተመለከተ እንዲሁም በዚህ ስምምነት ሽፋን ያገኘውን አላማ ተግባራዊ ከማድረግ እና ከዚህ ጋር ተያያዥ የሆኑ ተጓዳኝ እና ከሥራው ሂደት ጋር አግባብነት ያላቸውን ተግባራት ከመፈፀም የሚያግድ ምንም አይነት የሕግ ወይም ሌላ ገደብ የሌለ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

6.4 ለአፈር ምርመራ እና ለቅየሳ ስራ በፌዴራል መንግስት እና በክልል መንግስት የምርምር ማእከላት የሚገኙትን ፋሲሊቲዎችን በክፍያ እንዲጠቀም ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

6.5 ተከራይ በውል ባሉበት ግዴታዎች መሠረት መሬቱን በተቀመጡት የጊዜ ገደቦች ውስጥ ሳያለማ የቀረ እንደሆነ ወይም በተፈጥሮ ሃብቶች ላይ ጉዳት ካደረሰ ወይም የኪራይ ክፍያውን በወቅቱ ካልከፈለ አከራዩ በእነዚሁ ምክንያቶች የኪራይ ውሉን ለማቋረጥ ከወሰነ ይህንን ውሳኔውን ቢያንስ ከ6 ወራት ቀደም ብሎ በማስጠንቀቂያ መልክ ለተከራይ መስጠት አለበት፡፡ አከራይ ይህንን ጉዳይ ተከታትሎ ካላስታወቀ/ካላስፈፀመ ለተከራዩ ተጨማሪ የ 6 ወር ጊዜ ይሰጣል፡፡

6.6 ተከራይ በኪራይ ዘመኑ መሬቱን ሰላማዊና ከሁከት ነፃ በሆነ መንገድ ማልማት እንዲችል ከማንኛውም አመፅ፣ ረብሻ ወይም አስቸጋሪ የተፈጥሮ ክስተቶች ለመከላከል ከአቅም በላይ የሆኑ ሁኔታዎችን ሳይጨምር ያለክፍያ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## አንቀፅ 7

## የተከራየውን መሬት ስለማስረከብ

7.1 አከራይ ይህ ውል ከተፈረመበት ጊዜ አንስቶ በ30 ቀን ውስጥ የመሬቱን ፕላን ለተከራይ ያስረክባል፡፡

7.2 ተከራይ በፅሑፍ ተገልፆለትም ቢሆን በእርሱ በኩል በሆነ ምክንያት የመሬቱ ርክክብ ሳይፈፀም የቀረ እንደሆነ አከራይ በዚህ ምክንያት ምንም አይነት ኃላፊነት አይወስድም፡፡

7.3 በአንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2.2.2 የተጠቀሰው የመሬት ኪራይ የአንድ አመት ቅድሚያ ክፍያ እንደተፈፀመ የመሬት ርክክብ ይፈፀማል፡፡

7.4 የመሬቱ ርክክብ ተፈፃሚ የሚሆነው ወይም የሚፀናው ይህ ውል ከተፈረመበት በ15 ቀናት ውስጥ ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 8

## የውል እድሳት እና ማሻሻያ

8.1 ይህ የመሬት ኪራይ ስምምነት በተመሳሳይ የውል ቃሎች እና ሁኔታዎች መሠረት ሊታደስ ይችላል፡፡

8.2 ተከራይ ስምምነቱን ማደስ ከፈለገ የውል ዘመኑ ከመጠናቀቁ ከ6 ወራት በፊት ይህንኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

## አንቀፅ 9

## ውል የሚቋረጥባቸው ምክንያቶች

ይህ የመሬት ኪራይ ውል ስምምነት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች ሊቋረጥ ይችላል፡

9.1 የመሬት ኪራይ የውል ዘመን ሲያበቃ፣

9.2 አከራይ ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች መሬቱን ለተከራይ ሳያስረክብ የቀረ እንደሆነ፣

9.3 ተከራይ የስድስት ወር የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶም ቢሆን አከራይ በዚህ ውል ስር የተካተቱትን ማናቸውንም ግዴታዎች ወይም ቃልኪዳኖች ሳያከብር የቀረ እንደሆነ፣

9.4 ተከራይ አመታዊ የኪራይ እና ሌሎች የግብር ክፍያዎችን ለሁለት ተከታታይ አመታት ሳይከፍል የቀረ እንደሆነ፣

9.5 ተከራይ በአከራይ በኩል የ6 ወራት ቅድመ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ተከራዩ የውል ግዴታዎቹን በማክበር እንዲፈፅም ተጠይቆም ቢሆን ይህንን ሳይፈፅም የቀረ እንደሆነ፣

9.6 በንዑስ አንቀጽ 5.4 መሰረት ለተሻለ ነገር አከራይ የኪራይ ውሉን ለማቋረጥ ሃሳብ ያለው መሆኑን በመጥቀስ የ6 ወራት ቅድመ ማስጠንቀቂያ ሲሰጥ፣

9.7 በንዑስ አንቀጽ 3.6 መሰረት ለተሻለ ነገር ተከራይ የኪራይ ውሉን ለማቋረጥ ሃሳብ ያለው መሆኑን በመጥቀስ የ6 ወራት ቅድመ ማስጠንቀቂያ ሲሰጥ፣

## አንቀጽ 10
## የውል መቋረጥ ሂደት ውጤቶች

10.1 የመሬት ኪራይ ውሉ ሲቋረጥ ተከራይ የተከራየውን መሬት የውሉ መቋረጥ ተፈፃሚ ከሚሆንበት ቀን ጀምሮ በ6 ወራት ጊዜ ውስጥ ለአከራይ መመለስ አለበት፡፡

10.2 ይህ የኪራይ ውል ስምምነት በተከራዩ በዚህ ስምምነት በአንቀፅ 9.3 መሰረት እና በአከራዩ 9.6 መሠረት በማናቸውም ምክንያቶች በሚቋረጥበት ወቅት አከራይ በመሬቱ ላይ የተከናወኑትን ዋጋ ያላቸው ማሻሻያዎችና ወጪዎች በወቅቱ የገበያ ዋጋ ማንኛውም የተከራይ ዕዳዎች ከተከፈሉ በኋላ ለተከራይ ይከፍላል፡፡

10.3 ይህ ስምምነት ከላይ በአንቀፅ 9.4፣ 9.5 እና 9.7 ከተዘረዘሩት ምክንያቶች መካከል በማናቸውም መነሻነት ያቋረጠ እንደሆነ እንዲህ ባለው ምክንያት አከራይ ለተከራይ የሚከፍለው አይኖርም፡፡

10.4 ይህ የመሬት ኪራይ ውል በሚቋረጥበት ወቅት በመሬቱ ላይ ያሉ ንብረቶችን በድርድር ለመግዛት ለአከራይ ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡ አከራዩ ካልፈለገ ተከራይ ንብረቱን አንስቶ የመውሰድ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

## አንቀፅ 11
## ምዝገባ

ይህ የመሬት ኪራይ ስምምነት ስልጣን በተሰጠው አካል መመዝገብ እና መፅደቅ ግዴታ የለበትም ፤ የዚህ ውል ስምምነት ቅጅዎችና ግልባጮች ለአከራይ፣ ለተከራይ፣ ለወረዳ፣ ለፋይናንስ ጽ/ቤት፣ ለኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና ሌሎች አካላት በአከራይ በሚሰጥ ሸኚ ደብዳቤ አማካኝነት ለትብብር ያመች ዘንድ እንዲላኩ ይደረጋል፡፡

## አንቀፅ 12
## ገዥ ሕግ

በዚህ ስምምነት ስር ስራዎችን የሚገዛው የኢትዮጵያ ሕግ ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 13
## ከአቅም በላይ የሆኑ ሁኔታዎች

ከአቅም በላይ የሆኑ ሁኔታዎችን አስመልክቶ የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 14

## ሰላማዊ ለሆነ አጠቃቀም የተገባ ቃል

አከራይ በተከራየው መሬት ላይ ያለውን የባለቤትነት እና የንብረት መብቶች ያረጋግጣል። በመሆኑም ተከራይ መሬቱን ሰላማዊ በሆነ መልኩ በይዞታው እንደሚያቆይ እና ይህንንም ያለምንም ችግር ሊጠቀምበት እንደሚችል ያረጋግጣል።

## አንቀፅ 15
## የቀን መቁጠሪያ

ለዚህ ስምምነት ዓላማ የኢትዮጵያ ቀን መቁጠሪያ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

## አንቀፅ 16
## የስምምነቱ አባሪዎች

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሰነዶች የስምምነቱ አባሪ ሲሆኑ የውሉ አካል ተደርገው ይወሰዳሉ።

16.1 የተከራየው መሬት ሳይት ፕላን

16.2 የአካባቢ ጥበቃ ስነምግባር ደንብ

## አንቀፅ 17
## አለመግባባትን ስለመፍታት

ከመሬት ኪራይ ስምምነቱ ጋር በተያያዘ ወይም ስምምነቱን ተከትሎ በአከራይ እና በተከራይ መካከል አለመግባባት በሚከሰትበት ወቅት ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች አለመግባባቱን ሰላማዊ በሆነ መልኩ እና ለሁለቱም ወገኖች በሚጠቅም መልኩ ለመፍታት የሚችሉትን ጥረት ሁሉ ያደርጋሉ። እንዲህ ባለ ሁኔታ አለመግባባቱ ሊፈታ ካልቻለ ጉዳዩ በኢትዮጵያ የፌዴራል ፍ/ቤት የሚታይ ይሆናል።

## አንቀፅ 18
## ጽ/ቤት ስለማቀቋቋምና እና ማስጠንቀቂያዎች

18.1 ተከራይ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደ አስፈላጊነቱ ወይም ሥራዎቹን ለማከናወን በሚያመቸው መልኩ ጽ/ቤት ይመሰርታል ለአከራይም ያሳውቃል።

18.2 ከዚህ ስምምነት ተዋዋይ ወገኖች መካከል ለአንዱ የሚላክ ደብዳቤ እና ማስጠንቀቂያ በእንግሊዘኛ ወይም በአማርኛ ቋንቋ በተዘጋጀ ፅሑፍ አማካኝነት ይሆናል። እንዲህ ያለውም ፅሑፍ በአካል ወይም በዚህ ስምምነት መግቢያ ላይ በተጠቀሰው አድራሻ በፖስታ ይላካል።

Tigab Agro-Industry

## አንቀፅ 19

## ውሉ የሚፀናበት ቀን

ይህ የኪራይ ስምምነት ለ *25* አመታት ማለትም ከተፈረመበት *23/11/2003* ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡ ተፈፃሚነቱም በ *22/11/2028* ያበቃል፡፡

አከራይ
ግብርና ሚኒስቴር
ስም
ፊርማ
ቀን

ተከራይ
ጥጋብ አግሮ ኢንዱስትሪ
ስም (ወ/ሮ ሠውነት ዓለምነህ ባይነስ)ባለ ሀብት
ፊርማ
ቀን

እማኞች

| | ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|
| 1. | | | 03/12/2003 |
| 2. | | | 03/12/2003 |
| 3. | | | 03/12/2003 |